DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of School Improvement and Supports

የድህረ-ገጽ - አዲስና ማሻሻያዎች (Updates):

የማህበራዊ ሥራተኞች (Social Workers)፣ የትምህርት ቤት የስነ-አዕምሮ ባለሞያዎች፣ የትምህርት ቤት ካውንስለሮች እና የማህበረሰባችን የአዕምሮ ጤና አጋሮቻችን፤ አጋዥ-የሆነ አገልግሎቶችን - በቀለም-ትምህርት ውስጥ ካሉ ችግሮች ውስጥ ከመውጣት አንስቶ - እስከ ሕይወትን-የሚያናጉ ሁኔታዎችን እስከመቋቋም ድረስ ባሉ ነገሮች ላይ፣ በማንኛውም ምክንያት እርዳታን ለሚፈልጉ ተማሪዎች አገልግሎት ይሠጣል። ስለሚሰጡ አገልግሎቶች፤ መረጃዎችን በማጋራት - ሊገኙ የሚችሉ መመሪያዎች - እንደሚከተሉት ተገልጸዋል:

- ተማሪዎች የደረሰባቸውን ጭንቀት እና ቀውስ ለመቋቋም እንዲረዳቸው፣ የቴራፒ-ጣልቃ-ገብነቶችን ይሰጣል፤
- ከተማሪዎች ጋር ግንኙነትን ለመገንባት የሚረዳ፣ የአነስተኛ-ቡድን ክፍለጊዜዎችን ይመራል፤
- የአደንዛዥ ዕፅ መከላከል እና ጣልቃ-ገብነትን ይሰጣል፤
- ለተማሪዎች በትኩረታቸው እና ማስተዋል-በሚሰጧቸው ነገሮች ለመርዳት፣ ስልቶችን እና ችሎታዎችን ማቅረብ፤
- ተማሪዎችን በስራ-ላይ የሚውሉ የመረጃ-ምንጮች እንዲያገኙ በማድረግ - ቤተሰባቸው፤ ምግብ፣ ልብስ እና መጓጓዣ የሚያገኙበትን መንገድ በመስጠት መርዳት፤
- ሁሉን-አቀፍ የሆኑ ግምገማዎችን በማጠናቀቅ፣ የትምህርት ቤት ቡድኖችን በመረጃ-ስብስብ (data) ላይ የተመረኮዘ ውሳኔዎችን እንዲያደርጉ መርዳት

አስፈላጊ-የሆኑ እርዳታ እንዲገኝ ለመርዳት፤ የDCPS ትምህርት ቤት የአዕምሮ ጤና ቡድን - ዓለም-አቀፍ የመምራት ሂደት (referral process)ን ቀርጿል። ይህ ሂደት፤ በትምህርት ቤትዎ ውስጥ አንድ-ቅጽን ሞልቶ-በማጠናቀቅ፤ ሁሉንም የአዕምሮ ጤና እና የማማከር እርዳታዎችን እንዲያገኙ ያደርግላቸዋል። ይህ ቅጽ፤ ተማሪዎችን ለአገልግሎት ለሚመሩ አዋቂዎች ሲሆን፣ እና እራሳቸው አገልግሎቶች እንዲያገኙ ለሚጠይቁ ተማሪዎች፣ ሌላ-የተለየ ቅጽ አለ። ተገቢ-የሆነውን ቅጽ መሙላት እና ከእናንተ-ጋር ተገናኝቶ ባላችሁ ስጋቶች ላይ ለመወያየት እና በስምምነቶች (consent) እና በሌሎች ቅድመ-አገልግሎት መረጃ ላይ፣ መረጃዎችን ከሚሰጧችሁ - ከትምህርት ቤትዎ የባህሪይ ጤና አስተባባሪ ጋር በማጋራት ተነጋገሩ።

የመመራት (Referral) ቅጽ፤ (የራስ/self)

የመመራት (Referral) ቅጽ፤ (ሌላ)

1200 First Street, NE | Washington, DC 20002 | T 202.442.5885 | F 202.442.5026 | dcps.dc.gov